# የአለም ፖለቲካ-ኢኮኖሚና የኢትዮጵያ ህዳሴ

## በአቶ ዓለምነው መኮንን ብዕር ሲቃኝ

**ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ 04-06-17**

***መግቢያ***

ካለኝ ቅርበት አኳያ አቶ ዓለምነውን አንተ እያልሁ ብገልጸው እውነት ነው የምላችሁ ደስ ባለኝ ነበር፣ ሆኖም በሀገራችን ባህል መሰረት ትልቅ የፖለቲካ ስልጣን ላይ የሚገኝን ሰው አንተ እያለሉ መግለጽ አንድም እንደ መዘርጠጥ አሊያም አክብሮትን እንደ መንፈግ ተደርጎ ስለሚወሰድ በዚህ መጣጥፍ ውስጥ አቶ ዓለምነው መኮንንን በእጅጉ እየተናነቀኝም ቢሆን አንቱ እያልሁ ለመግለጽ ተገድጃለሁ፡፡ ብዙዎቻችን እንደምናስታውሰው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብአዴን/ኢህአዴግ አባላትና በአማራ ክልል ህዝቦች ዘንድ አቶ ዓለምነው መኮንን እየታወቁ የመጡት በአወዛጋቢ ንግግራቸው ብቻ ሳይሆን በጥሩ አንባቢነታቸውና አዳዲስ ሀሳቦችን በማመንጨት የተግባር መመሪያ ለማድረግ በመንቀሳቀሳቸውም ጭምር ነው፡፡

በተለይም በአንድ ወቅት በግሉ ፕሬስና በማህበራዊ ሚዲያው አካባቢ "የአማራን ህዝብ ሰድበው ለሰዳቢ ሰጡት" በሚል ሽፋን የእሳቸውን ግላዊ ስብዕና ለመግደል ጥረት ከመደረጉም በላይ በአሁኑ ወቅት እሳቸውና የስራ ባለደርቦቻቸው በፈታውራሪነት የሚመሩትን የፖለቲካ ድርጅት ከህዝብ ለመነጠል አጋጣሚውን መጠቀማቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ በዋነኛነት ለብአዴን አባላት በሚሰራጨው አብዮታዊ ዴሞክራሲ መጽሔት ላይ በሚያቀርቧቸው መጣጥፎች ቀደም ሲል ባልተለመደ ሁኔታ ጥልቅ ትንታኔ በመስጠትና ይህንኑም ትንታኔያቸውን በበርካታ ማጣቀሻዎች በማስደገፍ አሳማኝ ንድፈ ሀሳባዊ አቀራረብን ከአለማችንና ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም በመሞከራቸውም ይታወቃሉ፡፡

አሁን ደግሞ ፖለቲካ-ኢኮኖሚና የኢትዮጵያ ህዳሴ በሚል አብይ ርዕስ በዋነኛነት 405 ገጾችን የያዘ ዳጎስ ያለ መጽሀፍ በማሰጋጀት አሳትመው ቀደም ባለው ሳምንት በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ማስመረቃቸውን በመገናኛ ብዙሀን አማካኝነት በሰማን ማግስት በአዲስ አበባና አካባቢው ለምንገኝ ወገኖቻቸው ዕድሉ እንዲደርሰን ለማድረግ በማሰብ ይመስላል በብሔራዊ ትያትር አዳራሽ በድጋሚ ለማስመረቅ ዝግት ማድረጋቸውን በመስማታችን የዝግጅቱ ታዳሚ እንደምንሆን አስቀድመን አረጋገጥን፡፡ ስለሆነም የዚህ መጣጥፍ ዋና አላማም በመጽሀፉ ምረቃ ወቅት የነበረው ሁኔታ ምን ይመስለ እንደነበረ በአጭሩ መግለጽ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ ንባብን መሰረት በማድረግ በመጽሀፉ አቀራረብና ይዘት ላይም ያለኝን የተመጠነ ምልከታ በወፍ በረር ቅኝት ለተደራሲያን ለማሳየት መሞከር ይሆናል፡፡ መልካም ንባብ!!

***የመጽሀፉ ምረቃ ስነ-ስርአት ድባብ በብሔራዊ ትያትር አዳራሽ***

መጋቢት 9/2009 ዓ.ም ከላይ ርዕሱ የተጠቀሰው የአቶ ዓለምነው መኮንን መጽሀፍ በብሔራዊ ትያትር አዳራሽ እንደሚመረቅ አስቀድሞ ስለተነገረኝ እኔም በቅርብ የማውቃቸውን ሰዎች እንዲገኙ ጋብዤ በስአቱ በቦታው ተገኘሁ፣ በመሆኑም ድባቡ እጅግ

ደስ የሚል ሁኔታን ያንጸባርቅ እንደ ነበር ቀዳሚ ምስክር ለመሆንም በቃሁ፣ በእውነትም የመጽሀፍ ምረቃ መሆኑን ገና የቲያትር ቤቱ አዳራሽ በር ሲገባ ግራና ቀኝ በሁለት ጠረንጴዛዎች ላይ መጽሀፉ ተደርድሮ ታዳሚው እየተሻማ ሲገዛው መታየቱ የድጋሚ ምረቃውን ተፈላጊነት በእጅግጉ ያሳብቅ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን አቶ ዓለምነው መኮንን ብአዴን/ኢህአዴግ በሚመራው መንግስት ውስጥ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ሆነው ሳለ ባለ አምስት ኮከብ የሆኑትን ሸራተን አዲስን ወይም ካፒታል ሆቴልን አሊያም ራዲሰን ብሉን ወይም ኢሊሌ ሆቴልን ለምን አልመረጡም? እያልሁ ጥያቄዎችን ለማንሳት ብገደድም ምክንያታቸው ምንም ይሁን ምን ለእኔ ይሻኛው ውሳኔያቸው በእጅጉ ተመችቶኝ እንደነበር ከመግለጽ ግን አልቆጠብም፡፡ ይህን እንድል ያደረገኝ በአንድ በኩል ብሔራዊ ትያትር የጥበብና የጥበበኞች ቤት በመሆኑ የጥበብ ስራ ውጤትን በዚህ ቤት ማስመረቅ በራሱ ደስ የሚል ስሜት ነበረው፡፡

በሌላ በኩል ሁሉንም ዜጋ በእኩል አይን እየተመለከተ ተቀብሎ ያለ ልዩ መጥሪያ ካረድና አድሎዋዊ መስተንግዶን ከሚያስከትለው ፕሮቶኮል ነጻ አድርጎ ለመታደም የመጣው ሰው በእኩልነት እንዲስተናገድ ዕድልን የሚሰጥ መሆኑ ሌላኛው መልካም ገጽታው ነው፡፡ ስለሆነም እጅጉን የብሔራዊ ትያትር አዳራሽ በእጅጉ ተስማምቶኝ ስለነበር ተደስቸበታለሁ፣ በምረቃው ስነ ስርአት ላይ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንንና የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዶ/ር ሂሩትን ጨምሮ በርካታ የፌዴራል የመንግስት ባለስልጣናት ተገኝተው የነበረ ቢሆንም ነባሮቹ የብአዴን/ኢ.ኢ.አዴግ ከፍተኛ አመራሮች ግን እንዳልተገኙ ታዝቤያለሁ፡፡

እነዚህ ከፍተኛ አመራሮች በምረቃ ስነ ስርአቱ ላይ ለምን ሳይገኙ ቀሩ ለሚለው ጥያቄ ለጊዜው መልስ ባለማግኘቴ በሒደት እውነታውን ከደረስሁበት አንድ ሁለት ልልበት እችል ይሆናል፣ ለዛሬው ግን በዚህ ዙሪያ ከዚህ በላይ የምለው የለኝም፡፡ ይህም ሆኖ አዳራሹን ከአፍ እስከ ገደፉ የሞላው ወጣትና የእኔ አይነት ተራው ሰው መሆኑ በእውነት ነው የምላችሁ አስደስቶኝ ነበር፡፡ ምክንያቱም ርዕሰ ጉዳዩ ወቅታዊ ከመሆኑም በላይ አሁን ላይ ባለው የሀገራችን የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ግንዛቤ ላይ ተመስርቶ የአለምን ፖለቲካ በሰፊውና በጥልቀት ለመቃኘት የተሞከረበት መጽሀፍ ስለሆነ በወጣቱ ትውልድ በአጠቃላይና በድርጅቱ ደጋፊ ወጣት ምሁራን ላይ በተለይ ሁለንተናዊ ግንዛቤን በማሳደግ ረገድ የሚኖረው ፋይዳ እጅግ የላቀ ነው ብየ አምናለሁና፡፡

በተለይ ደግሞ እንደዚህ ያለ ዳጎስ ያለ መጽሀፍ አዘጋጅቶ ለማሳተም ቀርቶ ትናንሽ መጽሀፊትን ለማንበብ ጊዜ የለንም የሚሉ ፖለቲከኞችና ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት በብዛት በሚገኙባት አገር ውስጥ ተሁኔ ከፍተኛ ጊዜና ትኩረትን ከሚጠይቅ ፋታ የለሽ የስራ ዘርፍ ጎን ለጎን በርካታ መጽሀፍትን አንብቦ በንጽጽር ለመተንተን ፍላጎት ማሳየት ብቻ ሳይሆን የእረፍት ጊዜ መስዋዕት ማድረግን፣ የአእምሮ ዝግጁነትንና ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ሀላፊነት ውስጥ ገብቶ መገኘት በራሱ ትልቅ ነገር መሆኑ አሌ የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡ የጥረት ዉጤትንም እንዲህ በተግባር ማሳየት መቻል በራሱ ብዙም ስራ ሳይኖራቸው ስራ ይበዛብናል ለሚሉና ምንም ሳያነቡ አዋቂ ለመምሰል ለሚሞክሩ የዘመኑ ባለስልጣናትና ፖለቲካኞቻችን ጠቃሚ ትምህርት የሚሰጥ ይመስለኛል፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነገር ብቻ ብየ ማለፍ እፈልጋለሁ፣ አቶ ዓለምነው ውድ የሆነውን ጊዜያቸውንና በጥረታቸው የተጎናጸፉትን ሁለገብ ክህሎታቸውን እንዲሁም በትምህርትና በጥልቅ ንባብ ያሳደጉትን እውቀታቸውን ለተደራሲያን በመስጠት ብቻ ሳይወሰኑ የማንንም ባለሀብት ይሁን የልማት ድርጅት የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ ድጋፍ ሳይጠብቁ ይልቁንም ያላቸውን ውስን ጥሪት አሟጠው በመጠቀም መጽሀፉን ማሳተማቸውና ለስርጭትም ማዘጋጀታቸው በእርግጥም አርአያነት ያለው ተግባር ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ በዚህ ረገድ የአቶ ደመቀ መኮንንን አባባል ልዋስና "አንድያ ቤታቸውን በባንክ አስየዘው ባገኙት የብድር ገንዘብ መጽሀፉን አሳትመው ለተደራሲያን እንዳቀረቡ በአደባባይ ተገልጧልና"፡፡ ይህም ድርጊታቸው በስፖንሰር ማፈላለግ ሽፋን በመቶ ሽዎች ወይም በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ከሚሰበስቡ የዘመኑ ባለስልጣናትና ግለሰቦች የተለየ እርምጃ መውሰዳቸው በእርግጥም የሚያበረታታ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ሌላው ቀርቶ መጽሀፉን ለማስመረቅ ከውድ ባለቤታቸው ሰብለወርቅ አባተ ጋር ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ የአውሮፕላን ቲኬታቸውን በራሳቸው ገንዘብ ቆርጠው አዲስ አበባ ላይ የሚቀበላቸው የጓደኛ ተሽከርካሪ ብቻ መጠቀም መቻላቸው ሲታከልበት እውነትም አቶ ዓለምነው ከማንም ምንም ነገር ላለመነካካት ያደረጉት ጥረት አካል ነውና መጽሀፉን ለማስመረቅ ለምን የብሔራዊ ትያትር አዳራሽን መረጡ ለሚለው ጥያቄየም ምላሽ ማግኘት ችያለሁ፡፡

በሌላ አባባል በዚህ ዘመን በእሳቸው የስልጣን ደረጃ የሚገኝ ሰው ቀርቶ ከዛ በታች ባለ የስልጣን ደረጃ ላይ የሚገኝ ፖለቲከኛ ስልጣኑን ያለ አግባብ በመጠቀም የግል ጥቅሙን ሲያሳድድ በሚገኝበት ወቅት በዋነኛነት ለመንግስትና ለድርጅት ስራ በእጅጉ ጠቃሚ የሆነ መጽሀፍን አዘጋጅቶ ለማሳተምም ሆነ ለተደራሲያን ለማሰራጨት የግል ሀብትን መጠቀም ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡ በእርግጥ አቶ ዓለምነው መኮንን ቀደም ሲል ጀምሮ ሳውቃቸው ንጹህ ታጋይ፣ ቀና አስተሳሰብ ያላቸውና የተሟላ ስብእናን የተላበሱ ሰው መሆናቸውን ጠንቅቄ ባውቅም አሁን በፈሙት ፍጹም ከሙስና የጸዳ ተግባር ይበልጥ እንዳከብራቸውና እንድኮራባቸውም አድርጎኛል፡፡

ስለሆነም የዚህ አይነቱን ቅን፣ ለሀገሩ ተቆርቋሪና ያለውን ሁሉ አሟጦ ለመስጠት የሚተጋን ሰው በፖለቲካ አቋም መለያየት ቢኖርና የተለያየ አስተሳሰብ ብንይዝም እንኳ መጽሀፉን አንብበን ማበረታታት የሚኖርብን ይመስለኛል፡፡ ይህንን ሀሳባችንን ተግባራዊ የምናደርገው ደግሞ በመጽሀፉ ውስጥ ለማስተላለፍ የፈለጉትን መልዕክት በመጋራት ስለሆነ ሁላችንም ይህንን መልካም ተግባር ሳንውል ሳናድር ብንፈጽም አንድም የአቶ ዓለምነው ድካም ውጤታማ መሆኑን እናረጋግጣለን፣ ሁለትም ስለ ሀገራችን ፖለቲካ ኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን ስለ አለም ወቅታዊ ሁኔታ በቂ የሆነ እውቀት በመሸመት አጠቃላይ ግንዛቤያችንን እናሳድጋለን፣ በመሆኑም መጽሀፉን አሁኑኑ አግኝተን ልናነበው ይገባል እላለሁ፡፡

## በመጽሀፉ ላይ ያለኝ አጠቃላይ ምልከታ

መጽሀፉ በመጀመሪያው ምዕራፍ ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔን መሰረት ያደረገ ገለጻን በሰፊው ያቀረበ ሲሆን ለቀጣዮቹ ምዕራፎች መንደርደሪያ የሚሆን ግብአትን አካቶ ይዟል፣ በመቀጠልም ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔን ከተግባራዊ እንቅስቃሴ ጋር አዛምዶ ለማቅረብ የሞከረ፣ ለበርካታ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች በቂ ሊባል የሚችል መልስ እየሰጠ የመጣ በተለይም በፖለቲካው አለም ውስጥ እስከ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ደርሰው ስለኒዮ

ሊበራሊዝም ጽንሰ ሀሳበም ሆነ ስለ ሶሻል ዴሞክራሲ ልዩ ባህሪያት ከዛም አልፎ የእለት ከእለት ተግባራቸው መሰረት ስለሆነው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር ምንነት፣ በአጠቃላይም ስለሶስቱ የዴሞክራሲ አይነቶች አንድነትና ልዩነት እዚህ ግባ የሚባል እውቀት ሳይኖራቸው በነባር አመራሮች ድጋፍ ብቻ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ተቀምጠው ግፋ በለው ለሚሉት ብቻ ሳይሆን የተወሰነ ግንዛቤ ይዘው ብዙ እንደሚያውቁ ለሚያስቡ የፖለቲካ አመራሮችና የመንገስት ባለስልጣናት የተግባር መመሪያ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ይህም ሆኖ ይህን ጭምቅ ሀሳብ ከማጣቀሻዎቹ ጋር እያገናዘቡና ከተቻለም አለፍ እያሉ የሌሎች ምሁራን ስራዎችንም መዳሰስን በጠየቀ ንባብ መደገፍ እንዳለበት ይታመናል፣ ለዚህም ዋነኛዎቹ የመጽሀፉ ተደራሲያን የሆኑት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ግንባር ቀደም አባላትና ባለስልጣኖቻቸው ራሳቸውን በቅጡ ማዘጋጀት የሚጠበቅባቸው ይመስለኛል፣ ከሁሉም በላይ ግን ራስን ከወቅቱ አለማዊና ሀገራዊ ሁኔታ በተለይም ነባራዊ ሀቅ ጋር እያጣጣሙ የአመራርና የመፈጸም አቅምን በቀጣይነት ማሳደግን ስራየ ብለው ሊይዙት እንደሚገባ ከአቶ ዓለምነው መጽሀፍ ትምህርት ሊቀስሙ ይገባል፡፡ አጠቃላይ ሁኔታውን በዚህ መልኩ አስቀምጬ ሳበቃ በመጽሀፉ አቀራረብ፣ የቋንቋ አጠቃቀምና ይዘት ላይ የተስዋሉትን ውስንኖቶች የተወሰኑ ምሳሌዎችን በማንሳት ለማሳየት ጥረት አደርጋለሁ፡፡

### የመጽሀፉን አደረጃጀትና አቀራረብ በተመለከተ

እኔ እስከማውቀው ድረስ ክፍል የሚለው ርዕስ ምዕራፍ ከሚለው ርዕስ ሰፋ ያለ ሆኖ ሳለ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ምዕራፍ የሚለው በስሩ በርካታ ክፍሎችን እንዲይዝ መደረጉ ተገቢ ነው ብየ አላምንም፣ ይልቁንም መሆን የነበረበት የተገላቢጦሹ ነው፣ ምንያቱም በክፍል ስር በርካታ ምዕራፎች ሊኖሩ ይችሉ እንደሆነ እንጂ በምዕራፍ ስር ከንዑስ ምዕራፎች ያለፈ በርካታ ክፍሎች ሊኖሩ አይችሉምና ነው፡፡ ሌላው እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር የሚለው በልዩ ሁኔታ መታየት ሲገባው በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ግን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር የሚለው ነው በልዩነት የተቀመጠው፣ ይኽ ድግሞ ቅድሚያ ለስራስ ዋጋ ስጥ የሚለውን መርህ ወደ ጎን ያለ ያስመስለዋል፡፡

ምንም እንኳ አቶ ዓለምነው ይህንን ሁኔታ ቅድሚያ እንዲሰጡ ያደረጋቸው በብዛት የውጭ መጽሀፍትን በዋቢነት ከመጠቀማቸው ጋር ተያይዞ ሊሆን እንደሚችል ቢገመትም መጽሀፉ ኢትዮጵያዊ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ ጥርት ብሎ እስከተጻፈ ድረስ የዚህ አይነቱ አቀራረብ የተለመደ አይደለምና በወቅቱ መታረም ነበረበት፡፡ በሌላ በኩል በተለምዶ በአንድ መጽሀፍ ውስጥ ሊካተቱ ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ ምስጋናና መቅድም በቀዳሚነት ይገኙበታል፣ የምስጋና መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የሚሰጠው ገጽም ከሁሉም ቀድሞ መገኘት ሲገባው በመጽሀፉ መጨረሻ ላይ እንደዋዛ መወሸቁ ብዙም ያልተለመደ ብቻ ሳይሆን ተገቢ ቦታ ሊሰጣቸው የሚገቡ ሰዎችንና ተቋማትን አዎንታዊ አስተዋጽኦ በሚገባ እንዳይታወቅ ሊያደርግ ይችላልና እንደዛ ባይሆን ይመረጥ ነበር፡፡

ሌላው ከአቀራረብ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት የመቅድምና የመግቢያ አጻጻፍን የሚመለከተው ጉዳይ ነው፣ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ መቅድም ተብሎ የቀረበው የመጽሀፉ መግቢያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ካልሆነ በስተቀር መቅድም ሊያሰኘው የሚያስችል ይዘተ አላገኘሁበትም፡፡ በእኔ እምነት መቅድም በዋነኛነት መጽሀፉን ለመጻፍ ያነሳሳውን

ሁኔታ፣ በሒደቱ የተከሰቱ መልካምና ገፊ አጋጣሚዎች እንዲሁም የታለፉ ፈተናዎች በመጨረሻም የተደረሰበት ደረጃ እና የወሰደውን ጊዜ በአጭሩ በማመልከት ተደራሲያን ለካ ይሄም ኖርሏል እንዲሉ ለማድረግ የምንጠቀምበት ገጽ ነው ብየ አምናለሁ፡፡ እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያይዞ መታየት የነበረበት ሌላው ጉዳይ ደግሞ የግርጌ ማስታወሻና የዋቢ ጽሁፎች ዝርዝር በአንድ ላይ መቅረቡ ነው፡፡ በዚህ መጽሀፍ ላይ ሁለቱም በአንድ ላይ ተዘርዝረው የቀረቡበት ሁኔታ ታይቷል፣ የዚህ አይነት አቀራረብ ብዙም የተለመደ አይደለም ብቻ ሳይሆን ዋና ዋና የማጣቀሻ ጽሁፎችን በአግባቡ ለይተን እንዳንመለከት የሚያደርግ በመሆኑ ያን ታሳቢ ማድረግ ነበረበት፡፡ ይልቁንም የግርጌ ማስታወሻዎች በየገጹ ቢመለከቱና መጨረሻ ላይ ደግሞ የዋቢ መጽሀፍት ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተል ቢቀመጥ ኖሮ አንባቢ የተጠቀሰው ሀሳብ ከየትኛው መጽሀፍ ወይም ሰነድ ላይ እንደተወሰደ ለማረጋገጥም ሆነ ተጨማሪ ግንዛቤ ለማግኘት ቢፈልግ በቀላሉ ለማግኘት ያስችለው ስለነበር ይኸኛው አማራጭ ይበልጥ የተሻለ እንደነበር ከወዲሁ መገመት አይከብድም፡፡

ሌላው በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ያገኘሁት ለየት ያለ ነገር ደግሞ የኢታሊክስ አጠቃቀም ነው፤ በጥቅስ ውስጥ የሚቀመጡ ሀሳቦች በኢታሊክስ መልክ እንዲቀመጡ የሚደረገው በደራሲው አማካኝነት ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ በቀጥታ የተተረጎሙ ከሆነ ብቻ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ሆኖም በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ሁሉም በጥቅስ ውስጥ የሰፈሩ ሀሳቦች በኢታሊክስ መልክ እንዲቀመጡ ከመደረጉም በላይ ሁሉም በጥቅስ ውስጥ የገቡ ሀሳቦች እጅግ ደምቀው እንዲታዩ ተደርጓል፣ ይህንንም አቀራረብ ደራሲው ተሳስቶ ቢጠቀምበት እንኳ በዋነኛነት የአርትኦት ስራውን በሀላፊነት ያከናወኑት ሰዎች በጊዜው ሊያስተካክሉት በተገባ ነበር፡፡

### በመጽሀፉ ውስጥ የታየው የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ

ከቋንቋ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ አቶ ዓለምነው በሚገርም ሁኔታ የአማርኛ ቋንቋን በአግባቡ ስራ ላይ ማዋላቸውን በልበ ሙሉነት መመስከር እችላለሁ፣ እሳቸውም በመግቢያው ላይ አስቀድመው ለመግለጽ እንደሞከሩት አብዛሀኛው ሀሳብ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከተጻፉ መጽሀፍትና መጣጥፎች እየተሰደ የተተነተነ በመሆኑ በመጽሀፉ ውስጥ በርካታ የእንግሊዘኛ ቃላትን አገኛለሁ ብየ ጠብቄ ነበር፡፡ ሆኖም አቶ ዓለምነው የቻሉትን ያህል ጥረት በማድረጋቸው ከቋንቋ አጠቃቀም አንጻር የጎላ ስህተት ሳይፈጽሙ መቅረታቸውን ተመልክቻለሁ፣ እናም የዚህ አይነቱ ጥረት በእጅጉ ሊበረታታ ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡

ሆኖም ስራቸው አሁንም ከጉድለት የጸዳ አለመሆኑን አንዳንድ ምሳሌዎችን በማንሳት ለማሳየት ልሞክር፣ በቀላሉ ወደ አማርኛ ተመልሰው ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቃላት ወይም ሀረጋት በእንግሊዘኛ እንዳለ የተገለጹበት ሁኔታ ተሰተውሏልና ነው፡፡ ለምሳሌ ቶርቸር፣ ፊልድ ስቴትስ (ገጽ 9)፣ ኋይ ኔሽንስ ፌል (ገጽ 107)፣ ሲቪል ሰረቪስ በብዙ ገጾች ላይ፣ ካፒታል ከንዑስ ርዕሱ ጀምሮ፣ ማኑፋክቸሪንግ በተለዋጭነት እየገባ፣ ኦን ሶቭዮት ሶሻሊስት ወዘተ የሚሉት በአማርኛ ፊደላት ተጽፈው መግባታቸው በአንድ በኩል ቀጥተኛ የሆነ የአማርኛ ትርጉም ለመስጠት በማያስቸግሩበት ሁኔታ ለምን ጥቅም ላይ ዋሉ ያሰኛል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ያው የተለመደው የእንግሊኛ ቃላትን በየአጋጣሚው የመጠቀም ልማድ አቶ ዓለምነውንም ሙሉ ለሙሉ ያለቀቃቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከቋንቋ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ሌላው ጉዳይ የአማርኛ ቃላት ወይም ሀረጋት አጠቃቀማችን ላይ አልፎ አልፎ የሚስተዋል ግድፈት ወይም ጉድለት ነው፣ በዚህ ረገድ አቶ ዓለምነው በመጽሀፋቸው ላይ የተጠቀሙበትን አንድ ሀረግ ብቻ መዘን እንመልከት፣ ይኸውም "ድህነት አደር" የሚለው ሀረግ ነው፡፡

ይህ ሀረግ በተለምዶ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር፣ ላብ አደር፣ ወዘተ. እንደሚባለው ተደርጎ የተወሰደ ይመስላል፣ ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት ሀረጋት የአንድን የህብረተሰብ ክፍል የምጣኔ ሀብት መሰረት ወይም መተዳደሪያ አሊያም የስራ መስክ ለመግለጽ የሚያገለግሉ ሲሆን፣ ድህነት አደር የሚለው ሀረግ እስካሁን ድረስ በምንጠቀምበት የአማርኛ ቋንቋችን ውስጥ ትርጉም የለሽ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቀን ተቀን ግንኙነታችን ተጠቅመንበት የማናውቅና በአማርኛ ተናጋሪው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሀረግም አይደለም፡፡ ስለሆነም እንደዚህ አይነት ለአብዛኛው ተደራሲ ብዙም ትርጉም የማይሰጡ ሀረጋትን ወይም ቃላትን ከመጠቀም ይልቅ የተለመዱና ስሜት ሊሰጡ የሚችሉ ሀረጋትን ብንጠቀም የተሻለ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ በሌላ አነጋገር ለየት ያለ አቀራረብ የተጠቀምን መስሎን የምናስገባቸው ቃላት በአንድ በኩል ትርጉም የለሽ የሚሆኑበት አጋጣሚ ይፈጠራል፣ በሌላ በኩል የተደራሲያንን ንባብ ያደናቅፉልና አስቀድሞ ማረሙ ሳይሻል አይቀርም፡፡

**የመጽሀፉ ይዘት**

ይህ መጽሀፍ በአብዛኛው ሁሉን አቀፍና በርካታ ጉዳዮችን የዳሰሰ በመሆኑ በአንድ መጽሀፍ ውስጥ የበርካታ ዘርፎችን ልምድ፣ ክህሎትና እውቀትን ለማግኘት እድል ይሰጣል የሚል እምነት አለኝ፣ ሆኖም በርካታ ጽንሰ ሀሳቦችን በአንድ መጽሀፍ ውስጥ አጭቆ ለማቅረብ ከመሞከሩ ጋር ተያይዞ በአንድ በኩል የሀሳቦች መደጋገምን ሲጋብዝ በሌላ በኩል አንዳንድ መሰረታዊ ሀሳቦች በአጭሩ ተገልጸው እንዲያልፉ አድርጓቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ከደከሙ አይቀር ሰፋ ብለው ቢዳሰሱና በአዲስ መልክም ቢካተቱ ያልኳቸው የተወሰኑ ሀሳቦች እንዳሉ አምናለሁ፡፡ ቀጥሎ በሚገኙት አንቀጾች በምሳሌ እያስደገፍሁ ለማሳየት ልሞክር፡፡

የአለም ባንክ፣ የአለም የገንዘብ ተቋምና የአለም የንግድ ድርጅት አሉታዊ ተጽዕኖ ጠቅለል ባለ መልኩ የተገለጸ ቢሆንም በአፍሪካ አገሮች ላይ በአጠቃላይና በኢትዮጵያ ላይ ደግሞ በተለይ የነበረው አሉታዊ ተጽዕኖ ምን ይመስል እንደነበር በምሳሌ ተደግፎ ቢገለጽ የተሟላ ስዕል ይሰጥ እንደ ነበር መገመት ይቻላል፡፡ ሌላው ቀደም ሲል የነበረው የኦሮሞ የገዳ ስርአት በተወሰነ መልኩ የተጠቀሰ ቢሆንም አሁን ባለው ፌዴራላዊ አደረጃጀት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ብቻ ሳይሆን የፌዴራል መንግስት አተያይ ምን እንደሚመስል እንደመነሻ ሊያገለግል በሚችል መልኩ በጥልቀት አለመውሰዱስ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ሀሳብ ላይ የተወሰነ ነገር ቢባል ኖሮ ጥሩ ነበር፡፡

ከገጽ 107 አጋማሽ እስከ 112 አጋማሽ ድረስ ባሉት ገጾች ላይ ደግሞ ስለኢትዮጵያ ህዝቦች የትግል ሒደት የተቀመጠው ሀሳብ አጭር ከመሆኑ የተነሳ በተወሰኑ ገጾች ብቻ

ቀንብቦ ማስቀመጥ ከሀገራችን ተሞክሮ ጋር በማያያዝ ብዙ ትምህርት እንዳይገኝበት ያደረገ ይመስለኛል፡፡ ከዛም ባሻገር ይኸ ንዑስ ርዕስ በአገር ውስጥ ምሁራን ስራዎች ላይ ተመስርቶ ትንሽ ቢዳብር ኖሮ መልካም እንደነበር መገመት የይላል፣ በዚህ ረገድ የፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴንና የዶክትር አሰፋ ፍስሀ ስራዎችን በስፋት መጠቀም አለመቻሉ በእጅጉ ያስቆጫል፣ እንዳውም የአቶ አለምነው መጽሀፍ ከመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ከኢህአዴግ ጽሁፎች ውጭ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ምሁራን ስራዎችን ወደ ጎን የተወ ይመስላል፡፡

ምናልባትም የዶክትር ምህረት ደበበን መጽሀፍ (እሱም ቢሆን የታሪክ ወይም የፖለቲካ መጽሀፍ ሳይሆን በዋነኛነት በስነ አዕምሮ ጠና ላይ የተመሰረተ ልቦለድ እንደሆነ ነው የሚታወቀው) አንድ ጊዜ እንዲሁም አቶ አለሙ አበበ የተረጎሙትን መጽሀፍ ሁለት ጊዜ በዋበነት ጠቅሰዋቸው ካልሆነ በስተቀር የሀገራችን የታሪክና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን እንዲሁም ታዋቂ የምጣኔ ሀብት ሞያተኞች ስራዎች አለመዳሰሳቸው ለራሳችን የምንሰጠውን ትኩረት አናሳነት በግልጽ ያመለክታል፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንድ ምሳሌ ልጨምርና የችግራችንን ስፋት ለማሳየት ልሞክር፣ የደቡብ ኮሪያ መሪዎች ችንግዶ የምትባል መንደር ነዋሪዎችን እንቅስቃሴ ከተመለከቱ በኋላ መልካም ስራዎቻቸውን በተሞክሮነት ቀምረው ለሌሎች አካባቢዎች ማስተላለፋቸውን በምሳሌነት አንስተው ሰፊ ትንታኔ አቅርበዋል፣ የሚገርመው ነገር አቶ አለምነው ሩቅ ምስራቅ ኤዥያ ድረስ ሳይጓዙ እሳቸው በሚያስተዳድሩት ክልል ውስጥ እሳቸው ከሚኖሩበት ከተማ 77 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኙት አውራምባዎች ደቡብ ከሪያ ከምትገኘው መንደር በተሻለ ደረጃ ሊቀመርላቸው የሚችል መልካም ተሞክሮ እንዳላቸው ጠጋ ብለው በመመልከት በጥሞና ቢመረምሩት ኖሮ ምንኛ ጠቃሚ ትምህርት ባገኙ ነበር፡፡

በተለይም ከታታሪነት፣ ከፆታ እኩልነት፣ ከስራ ወዳድነት፣ ከመተጋገዝና ከመደጋገፍ ጋር ተያይዞ ከአውራምባዎች ብዙ መማር ይቻል የነበረ ቢሆንም ነብይ በአገሩ አይከበርም ወይም በእጅ የያዙት ወርቅ ሆነና ነገሩ ሌላ ፍለጋ አቶ ዓለምነው ብዙ ደከሙ፡፡ ሌላው ትኩረት ሊሰጣው የሚገባው ነገር ኪራይ ሰብሳቢ የሚለው ቃልና ሀረግ ሲሆን ይህ ሀረግ በመጽሀፉ ውስጥ እዚህም እዛም ተደጋግሞ ተጠቅሷል፣ ሆኖም ትርጉሙ ምን እንደሆነ፣ ታሪካዊ አመጣጡና አሁን ላይ በሀገራችን ያለበት ደረጃ ግምት ውስጥ ገብቶ በሚገባ ቢተነተን እግረ መንገዱን በዚህ ቃል ወይም ሀረግ ላይ በበርካታ ሰዎች ዘንድ የተፈጠረውን ብዥታ መግፈፍ ይቻል ነበር፡፡

በእኔ እምነት ይኸ ሀረግ ለመባል የተፈለገውን ሀሳበ በትክክል የሚያስተላልፍ ሆኖም አላገኘሁትም፡፡ እንዳውም የእንግሊዘኛውን አረፍተ ነገር ማለትም (Rent seeking) የሚለውን ቃል በቃል ለመተርጎም ከመፈለግ የመጣ አቀራረብን መሰረት አድርጎ የተፈጸመ ስህተትም ይመስለኛል፣ ሌላው በምዕራፍ ሁለት ክፍል ሁለት በተለይም 2.3 ወይም ከገጽ 127-129 አጋማሽ ድረስ ያለው ሀሳብ ቀደም ብለው ባሉት ገጾች በሚገባ የተገለጸ ስለሆነ እንዲሁም ክፍል ስድስት ማለትም ከገጽ 373 እስከ 377 የተቀመጡት ሀሳቦች ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የተደገሙ በመሆናቸው በድጋሚ መካተታቸው አስፈላጊ አልነበረም፡፡

ሌላው ከመጽሀፉ ገጽ 147-149 በተለይም በ5.3 እና በ5.4 ስር የሚገኙት ንውሳን ርዕሶች ተቀያይረው ቢቀርቡ ይበልጥ ስሜት ይሰጡ እንደነበር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፣ ምክንያቱም በመርህ ደረጃ የመንግስት ጣልቃ ገብነት የመጨረሻ አማራጭ ሆኖ መታየት ስላለበት፡፡ እንዲሁም በ5.4 ላይ የተቀመጡት ሁለት ትልልቅ ሀሳቦች ከሁለት ተከፍለው በሚገባ መተንተን ነበረባቸው፣ ይኸውም በአንድ በኩል የሁለቱም ጽንሰ ሀሳቦች መነሻና መድረሻ የተለያየ ከመሆኑ አንጻር ራሳቸውን ችለው ቢዳሰሱ መልካም ይሆን ነበር፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ንዑስ ርዕስ ለህብረት ስራ ማህበራት ሰፊ ሽፋን ሰጥቶ ስለ አክሲዎን ማህበራት ምንም ያልተባለበት ሁኔታም ስለተፈጠረ ቀላል የማይባል ክፍተት እንዲኖር አድርጓል፡፡

ልብ ብሎ ለሚመለከት ሰው በሀገራችንም ሆነ በቀረው አለም የአክሲዎን ማህበራት ሚና እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል፣ ለምሳሌ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን እየታየ ያለውን የኢንቨስትመንት ሁኔታ ስንመለከት የአክሲዮን ማህበራት ድርሻ እጅግ ጉልህ ሆኖ እናገኘዋለን፣ በዚህ ረገድ በዋነኛነት የአክሲዮን ማህበራት በስፋት የተሳተፉባቸውን የባንክ፣ የኢንሹራንስና በሪል ስቴት ልማት ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ኩባንያዎችን ወቅታዊ እንቅስቃሴ ብንመለከት የድርሻቸውን ጉልህነት መገንዘብ እንችላለን፡፡ ስለሆነም የአክሲዮን ማህበራት ሚና ራሱን በቻለ ንዑስ ርዕስ በሚገባ ቢተነተን መልካም ይሆን ነበር እላለሁ፡፡

በዚህ መጽሀፍ ወስጥ ቅድመ 1983 ኢትዮጵያ የነበረው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ላይ በተመጠነ መልኩም ቢሆን ዘርዘር ያለ ሀሳብ መቅረብ ነበረበት፣ ስለሌሎች አገሮች ቅድመ ታሪክ ሰፊ ሽፋን እየሰጡ መጥተው የራስን ማሳነስ ለራስ ሲቆርሱ የሚለውን አባባል የሚቃረን ሆኖ አግኝቸዋለሁ፣ በተለይም ለዋነኛ ተደራራያኑ በንጉሱ የመጨረሻ የስልጣን ዘመን በውጭም ይሁን በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ተጀምረው የነበሩት ዘመናዊ እርሻና የኢንዳስትሪዎች ማቆጥቆጥ፣ በደርግ ጊዜ በእጅጉ ተስፋፍቶ የነበረው የመንግስት እርሻና የህብረት ስራ ማህበራት እንቅስቃሴ በአዎንታም ሆነ በአሉታ ብዙ ሊባልላቸውና ጠቃሚ የሆነ ትምህርትም ሊወስዱበት የሚገባ ጉዳይ እንደነበር በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ ረገድ ጠቃሚ ልምድም ሆነ ትምህርት ከውጭ ብቻ ይገኝ ይመስል የራስን ወደ ጎን በመተው የውጭዎች ላይ መመስረት “የራስን ጥሎ የሰው አንጠልጥሎ” ሊያሰኝ ይችላልና በአግባቡ ቢታሰብበት መልካም ሳይሆን አይቀርም፡፡ ሌላው በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ስለዴሞክራሲ ጽንሰ ሀሳብም ሆነ አስፈላጊነት ላይ ብዙ ተብሏል፣ ሆኖም በኢህአዴግ የሚመራው የሀገራችን መንግስት ባለፉት 26 አመታት ከዴሞክራሲ ጽንሰ ሀሳብ አተገባበር ጋር ተያይዞ ያለበት ሁኔታ በምሳሌ ተደግፎ እንዲሁም እየገጠሙት የሚገኙት ተግዳሮቶች በምሳሌ ተደግፈው ቢገለጹ መልካም ትምህርት ይገኝበት ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሌላው ስለዴሞክራሲ ሲወሳ የምርጫ አፈጻጸምና የምርጫ አይነቶችን በአግባቡ መርጦ ጥቅም ላይ የማዋሉ ጉዳይ ጎልቶ መነሳቱ አይቀርም፣ በዚህ ረገድ ስለ ምርጫ አስፈላጊነትና ከዴሞክራሲ ጋር ያለውን ቀጥተኛ ተዛምዶ በተመለከተ በመጽሀፉ ሰፋ ውስጥ ያለ ማብራሪያ ቀርቧል፣ ሆኖም በአንድ በኩል በሀገራችን እስካሁን ድረስ ከተካሄዱት ምርጫዎች ምን ትምህርት አገኘን በሚለውና የተለያዩ የምርጫ ማስፈጸሚያ ስልቶችን መርጦ ስራ ላይ በማዋል ረገድ የታየው ክፍተት ከሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ

መብቶች ትግበራ ሒደት አኳያ የሚኖራቸውን አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽዕኖ መዳሰሱ ትርጉም የነበረው ይመስለኛል፡፡

ሆኖም መጽሀፉ ይህን ሁኔታ በለሆሳስ የዘለለው ይመስላል፣ በተረፈ በአጠቃላይ ሲታይ በመጽሀፉ ውስጥ አንዳንድ የተደጋገሙ ሀሳቦች ያሉ ቢመስልምና የተወሰኑ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ጉዳዮች በአግባቡ ሳይዳሰሱ የቀሩ ቢሆንም ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔ ከተግባራዊ እንቀስቃሴ ጋር ተገናዝቦ የቀረበበት ስለሆነ ጠቃሚ ትምህርት እንደሚገኝበት ይታመናል፡፡ በሌላ አነጋገር አቶ ዓለምነው ያቀረቡልን መጽሀፍ ሰፋፊ ሀሳቦችን በአንድ ላይ አካቶ ከመቅረቡ ጋር ተያይዞና ይህ መጽሀፍ የመጀመሪያ ስራቸው በመሆኑ የሚስተዋሉ መለስተኛ ጉድለቶች ቢኖሩበትም ተጠቃሎ ሲታይ የሀገራችን ፖለቲካ ኢኮኖሚ በአጠቃላይና ኢህአዴግ እየተከተለው ያለውን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከሌሎች በምን እንደሚለይ በዝርዝር ለማየት የሚያስችል ስለሆነ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ሊነበብ የሚገባው መጽሀፍ ነው፡፡